# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 289 ህዳር 13 2006 ገጽ 1


አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ በሳዉዲ አረቢያ በሚገኙ ወገኖቻችን ላይ በሚደርሰው ጥቃት ክፉኛ ተቆጥቷል። በዚህ የመከራና ጭንቅ ሰዓት ለወገኖቻችን ለመድረስ የሚቻለውን ጥረት ሁሉ ማድረግ እንዳለብን ያምናል። አባላቱ በነብስ አድን ርብርብ በግንባር ቀደምትነት እንዲሳተፉ መመሪያ አስተላልፏል። ይህ አጣዳፊ ሆኖም ጊዜዓዊ መፍትሔ ነው። በግንቦት 7 እምነት የችግሮቻችን ሰንኮፍ ያለው አዲስ አበባ ነው።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## ፋሽስት ወያኔ በጅዳ የሚገኘውን ቆንስላ ጽ/ቤቱን ላልተወሰነ ጊዜ መዘወጋቱን አስታወቀ

በሳውዲ አረቢያ ሪያድ በተለያዩ ቦታዎች የወገኖቻችን ስቃይ ዋይታና ግድያ አሁንም አላቆመም፤ በእያንዳንዷ ደቂቃ ምን ይፈጠር ይሆን በማለት በጭንቅ በጥብ ውስጥ የሚገኙ ወገኖቻችን ወደ ሀገራቸው የመመለሳቸው ተስፋ አይሎ ባለበት በአሁኑ ሰአት ፋሽስት ወያኔ አገልግሎት እንደማይሰጥ በማስታወቅ የጅዳውን ቆንስላ ጽ/ቤቱን መዝጋቱን በማስታወቂያ መግለጹ ከወደ ሳዉዲ አረቢያ እየተሰማ ነው።

በዓለም ዙሪያ የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን በወገኖቻቸው ላይ እየደረሰ ያለውን መስመር የሳተ ግፍና በደል ለማስቆም፤ በያሉበት ድምጽ ለሌላቸው ወገኖቻችን ድምጽ በመሆን የሳውዲውን መንግስት በዓለም ዙሪያ በማጋለጥና የዲፕሎማሲ ውጥረት ውስጥ ለመክተት እየጣሩ ባሉበት ባሁኑ ሰአት፤ ፋሽስት ወያኔ የአንበሳውን ድርሻ መጫወት ሲገባው በጅዳ የሚገኘውን ቆንስላ ጽ/ቤቱን መዝጋቱ ብዙዎችን አሳዝኗል። ወደ ሀገራችን እንመለሳለን የሚል እንጥፍጣፊ ተስፋ ሰንቀው እየጠበቁ የነበሩ ተጎጂ ወገኖቻችንንም ተስፋ የሰበረ እንደሆነ ታውቋል።

"በአሁኗ ሰአት ወገኖቻችን በሞትና በሂዎት መካከል ተይዘው በርሃብ በጥምና በብርድ እየተሰቃዩ ይገኛሉ" የሚሉ አንዳንድ ወገኖች "ፋሽስት ወያኔ ለዜጎቹ የሚያስብ ቢሆን ኖሮ ዓለመቀፋዊ እገዛ በመጠየቅ አፋጣኝ ርዳታ መስጠት በተገባው ነበር፤ እያደረገው ያለው ግን የነበረውን እንኳ መዝጋት ነው" ካሉ በኋላ "ስለ እኛ የሚቆምና የሚያግዘን መንግስት የሚባል አካል እንደሌለ ራሳችንን እናሳምንና ባቅማችንና በቻልነው ሁሉ ለወገኖቻችን ራሳችን እንድረስላቸው" ይላሉ።

ከዚህ በፊት በቀደመው የፋሽስት ወያኔ የጫካ ዘመን ወቅት ባስር ሽዎች የሚቆጠር የትግራይ ወገናችን በርሃብ ሲረግፍ፤ ፋሽስት ወያኔ በርሃብ እያለቀ በነበረው ወገናችን ስም ከዓለም ዙሪያ የተቀበለውን የትየለሌ ርዳታ ከችግረኛው አፍ እየነጠቀ ለግል ጥቅም በአውሮፓ በሚገኙ ባንኮች ማስቀመጡን የሚያስታውሱ ሌሎች ወገኖች ደግሞ "ወያኔዎች ከራሳቸው በቀር ሌላ ዘመድ የላቸውም ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## የወያኔ የግድያ እቅድ መክሸፍ ለሁመራና ወልቃይት ጸገዴ ወጣቶች ችግር ፈጠረ

ፋሽስት ወያኔ 'ወያኔ አ ሚሊኒየም' ብሎ ሰይሞት የነበረውና በአቶ አንዳርጋቸው ፅጌና የግንቦት 7 ሕዝባዊ ሃይል አመራሮች ላይ የተጠነሰሰ የግድያ እቅድ ከከሸፈ ወዲህ ህዝባዊ ሃይሉ ይገኝበታል ተብለው በተጠረጠሩት አጎራባች ወረዳዎች በሚገኙ ወጣቶች ላይ የተጠናከረ አሰሳ በማድረግ ወጣቶችን በማሰር ላይ መሆኑን ከቦታው የደረሰን መረጃ ይጠቁማል። ፋሽስት ወያኔ ልክ እንደቆሰለ አንበሳ እዚህም እዚያም በፍርሃት በመንደርደር በሁመራና በወልቃይት ጸገዴ የሚገኙ ወጣቶችን እያሰረ ይገኛል። ድርጊቱ ብዙዎችን እንዳሳሰበ የተገለጸ ሲሆን ለጉዳዩ ቅርበት ያላቸው ወገኖች ባካባቢው የሚገኙ ወጣቶች ሕዝባዊ ሃይሉ እየገኘው ባለው ስምና ዝና ተስበው ሊቀላቀሉ ይችላሉ ብሎ የሰጋው ወያኔ ይህን የእስር ርምጃ እየወሰደ እንደሆነ ይጠቁማሉ።

ባካባቢው እያየው ባለው ነባራዊ ሂዎት ያልተደሰተው ወጣት፣ የነገ ተስፋየ ምንድን ነው ብሎ መልስ ያጣው ወጣት፣ ከትላንት ዛሬ፣ ከዛሬ ነገ ቀስ በቀስ እየሞተ መሆኑን የተረዳው ወጣት እንኳን ከተጠናከረ ድርጅት ጋር መቀላቀል ይቅርና በራሱም ጠንካራ የተቃውሞ ድርጅት ሊያቃቁም ይችላል የሚሉ ሌሎች ወገኖች ደግሞ "የህ አይነቱ የፋሽስት ወያኔ ድርጊት ወጣቱን የበለጠ ተቃዋሚ ያደርገዋል እንጂ አያለዝበውም"። ለዚህም ነው ባሁኑ ሰአት ግንቦት 7 ሕዝባዊ ሃይል ከመቼውም ጊዜ በላይ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ታጋይ እየጎረፈለት መሆኑ የሚሰማው ይላሉ። ግንቦት 7 ሕዝባዊ ሃይል ፋሽስት ወያኔን በማስወገድ ሕዝቦቿ በመከባበር የሚኖሩባት ኢትዮጵያን ለመገንባት የሚደረገውን ሂደት ለማገዝ በትጥቅ ትግል ወያኔን ለመፋለም ዝግጅት እያደረገ ያለ የተቃውሞ ድርጅት ነው።

## አዜብ ህወሀትን ለመልቀቅ ማመከቻ ማስገበቷ ተሰማ

የቀድሞዉ ጠ/ሚኒስቴር ባለቤት የሆነችዉና የሙስናዋ እመቤት በመባል የምትታወቀዉ አዜብ መስፍን ከወጣትነት እድሜዋ ጀምሮ የገለገለችዉን ህወሀት ፓርቲ በቃኝ ብላ ለመተዉ ለፓርቲዉ ማ/ኮሚቴ የመልቀቂያ ደብዳቤ ማስገባቷን ዉስጥ አዋቂ ምንጮች አስታወቁ። ከባለቤቷ ከመለስ ዜናዊ ህልፈት በኋላ በፓርቲው የነበራት ተሰሚነትና የበላይነት እየተሸረሸረ በመምጣቱ፤ ከኤፈርት ሃላፊነቷ ሳትወድ በግድ በመነሳቷና እንዲሁም ጓግታለት የነበረው የአዲስ አበባ ከንቲባነት ስልጣን በማጣቷ፣ የተበሳጨችዉ አዜብ ተስፋ መቁረጥ መጀመሯ ፓርቲውን ለመልቀቋ ዋና ምክንያት እንደሆነ ምንጮቹ ተናግረዋል። ከዚህ በተጨማሪ አዜብ የምትተማመንባቸዉ አብዛኞቹ የህወሀት ባለስልጣኖች ከስልጣን ተባርረዉ መታሰራቸዉና እንዲሁም በስብሃት ነጋ ቡድን እየተወሰደባት ያለው ፖለቲካዊ የበላይነት መቋቋም ስለተሳናት ከፓርቲው በግዜ መሰናበቷ ሌላ አማራጭ የሌለዉ መሆኑን በቅርብ የሚያዉቋት ሰዎች በመናገር ላይ ናቸዉ። የህወሀት ማዕከላዊ ኮሚቴ በቅርብ ቀን ዉስጥ ተሰብስቦ የአዜብ መስፍንን ጥያቄ እልባት እንደሚሰጠዉ የጠቆሙት ምንጮች ከዚሁ ጋር አያይዘው ጥያቄው ተቀባይነት ካገኘ አዜብ በሲውዲን ወይም አሜሪካ ቨርጂኒያ ግዛት ዉስጥ በገዛቸዉ መኖሪያ ቤት ለመኖር ጓዟን እንደምትጠቀልል አመልክተዋል። ይህ በእንዲህ እንዳለ ዘረኛዉና ለብዙ ሰላማዊ ዜጎች ሞት ተጠያቂ የሆነዉ ጄ/ል ሳሞራ የኑስ ከኢታማጆር ሹምነቱ ቦታ ተነስቶ በምትኩ በቅርቡ የሌፍቴናንት ጄኔራልነት ሹመት የተሰጠዉ ጄ/ል ዮሃንስ ገ/መስቀልን ሊተካ እንደሚችል አዲስ አበባ ዉስጥ የሚገኙ ወታደራዊ ቃል አቀባዮቻችን ገለጹ።

## የፌደራል ፖሊሶች ሳዑዲ አረቢያ ኤምባሲ ፊት ለፊት የተቃዉሞ ስልፍ የወጡ ኢትዮጵያዉያንን ደበደበ

ሳዑዲ አረቢያ ዉስጥ በወንድሞቻቸዉና በእህቶቻቸዉ ላይ እየደረሰ ያለዉ በደልና ሰቆቃ አንገብግቧቸዉ ቁጣቸዉን ለመግለጽና የሳዑዲን መንግስት ለመቃወም በሳውድ አረቢያ ኢምባሲ ፊት ለፊት ተቃውሞዋቸውን ለመግለጽ የወጡ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ህጻን' ወጣትና ሽማግሌ ሳይባል በፌደራል ፖሊሶች እንደተደበደቡ ከአዲስ አበባ የደረሰን ዜና አስረዳ። በዚህ የሰማያዊ ፓርቲ በጠራው ሰላማዊ ሰልፍ ከተደበደቡት ሰዎች ሌላ የሰማያዊ ፓርቲና የአንድነት ፓርቲ አመራሮችና አባላት መታሰራቸዉ ታዉቋል። በዚህ ወያኔ እመራዋለሁ የሚለዉን ህዝብ እንደ ጠላት ቆጥሮ ባጠቃበት አጋጣሚ ከ100 በላይ ሰዎች የታሰሩ ሲሆን የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪና በየክልሉ የሚኖረዉ ህዝብ በወያኔና በሳዑዲ መንግስት ላይ ቁጣዉንና ተቃዉሞዉን እየገለጸ መሆኑ ታዉቋል።

የሰማያዊ ፓርቲ መሪዎች፤ አባላትና ደጋፊዎች ከፓርቲዉ ጽ/ቤት ተነስተው ወደ ሰላማዊ ሰልፉ ቦታ ሲሄዱ 4 ኪሎ የኦሮሚያ ሲቪል ሰርቪስ ቢሮ ጎን በሚገኘው ወታደራዊ ገራዥ መታሰራቸውን የታወቀ ሲሆን ከመታሰራው ቀደም ብሎ ከፖሊስ ጋር እንሂድ አትሄዱም በሚል ጭቅጭቅ ላይ እንደነበሩ ተሰምቷል። ሌሎች የፓርቲው አባላትና አመራሮች ተበታትነው ወደ ሳውዲ አረቢያ ኤምባሲ በመሄድ ላይ እያሉ ፖሊስ ከፈተኛ መጎሳቆል ያደረሰባቸዉ ሲሆን በተለይ አንዲት ሴት ክፉኛ በመመታቷ ለህይወቷ እንዲያሰጋ ለማወቅ ችለኛል። አንድ አስተያየት ሰጪ አንደተናገሩት "በሰው አገር ወገኖቻችን ላይ የደረሰውን ለመቃወም ወጥተን ተመሳሳይ ስቃይ አስተናገድን" ብለዋል። የሰማያዊ ፓርቲ የህዝብ ግንኙነት ሃላፊ የሆነው ወጣት ብርሀኑ ተክለያሬድ ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## በሳውድ አረቢያ በኢትዮጵያውያን ላይ የደረሰውን ጥቃት የሚቃወሙ ሰልፎች እንደቀጠሉ ነው

በሳውድ አረቢያ ህጋዊ የመኖሪያ ፈቃድ የላቸውም በሚል የሳውዲ ፖሊሶች እና ወጣቶች በኢትዮጵያውያን ሴቶች፣ ህጻናትና ወንዶች ላይ የፈጸሙትን የሰብአዊ ሙብት ጥሰት በመቃወም በተለያዩ የውጭ አገራት የሚካሄዱት የተቃውሞ ሰልፎች እንደቀጠሉ ሲሆን፣ ባለፈዉ ሀሙስና ዐርብ ስዊዘርላንድ በርንና አሜሪካ ዋሺንግተን ዲሲን ጨምሮ በጠለያዩ የአዉሮፓ፤ የአሜሪካና የመካከለኛዉ ምስራቅ አገሮች ዉስጥ የሚኖሩ በተካሄደው ኢትዮጵያውያኑ ስሜታቸውን መቆጣጠር እስኪሳናቸዉ ድረስ በስፋት ወጥተዉ ቁጣቸዉን ሲገልጹ ዉለዋል። በዚህ ከፈተኛ የኢትዮጵያዊነት ስሜት በታየበት ሰልፍ ኢትዮጵያውያኑ የሳውዲን መንግስትና የወያኔን አገዛዝ የሚያወግዙ መፈክሮችን እያሰሙ ወደ ሳውዲ ኤምባሲ ያቀኑ ሲሆን፣ ፖሊስ ከዘጋጀላቸው የመቃወሚያ ክልል በማለፍ በሳውዲ ኢምባሲ አቅራቢያ የተቃውሞ ድምጻቸውን አሰምተዋል።

( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## በሳውዲ ለሚገኙ ወገኖቻችን በአፋጣኝ እንድረስ፤ በወያኔ ላይ በጋራ እንነሳ!!!

በሳውዲ አረቢያ በሚገኙ ወገኖቻችን ላይ እየደረሰ ያለው መጠን የለሽ የሙብት ጥሰት ለመቃወም በተለያዩ የዓለም አገራት የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን በየአገራቱ የሚገኙ የሳውዲን ኢምባሲዎችን በተቃውሞ እያጨናነቁ ነው። በወገኖቻችን ላይ እየደረሰ ባለው ዘግኛኝ በደል የተሰማቸውን ጥልቅ የመጠቃት ስሜት ኢትዮጵያን በተቃውሞ ሰልፎቹ ላይ በሚያሰሟቸው መሪር የሐዘን እንጉሮችና የቁጭት ንግግሮች እየገለፁ ነው። ከሐዘንና ቁጭት ባለፈም ለበደል ለተጋለጡ ወገኖቻችን አስቸኳይ ሰብዓዊ ርዳታ ለማድረስ እና የዲፕሎማሲ ድጋፍን ለማሰባሰብ ዓለም ዓቀፍ ግብረ ኃይል ተቋቁሞ ሥራውን ጀምሯል።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ይህንን ዓለም ዓቀፍ ጥረት ለመደገፍ በውጭ አገራት የሚገኙ አባላቱ ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርጉ መመሪያ አስተላልፏል።

ይህ ሁሉ በውጭ አገራት እየተደረገ ያለ ጥረት ነው። ኢትዮጵያዊያን ባሉበት አገራትና ከተማዎች ሁሉ በዚህ ጉዳይ ላይ በአንድነት መንቀሳቀሳቸው የሚያስደስት ነገር ነው። ሌላው ቀርቶ በሳዉዲ ዋና ከተማ ሪያድ ውስጥ እንኳን ኢትዮጵያውያን የሳውዲን መንግሥት ተቃውመው ሰላማዊ ሰልፍ ወጥተዋል።

የሳውዲ መንግሥት በኢትዮጵያ ስደተኞች ላይ የያዘውን ጨካኝ አቋም እና በመንግሥት እውቅና በወገኖቻችን ላይ እየደረሰ ያለውን በደል መቃወም ያልተቻለው በኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ ነው። በኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ!!! ይህ እጅግ ያማል፣ ልብን ያደማል።

ወያኔ የሳውዲ የንግድ ሸሪኮቹን ለማስደሰት የፈንሳይን ግማሽ የሚያህል ለም መሬት በነፃ መስጠቱ በቂ አልመሰለውም። በአገራቸው ኢትዮጵያዊያንን ሲጨፈጭፉ፣ ሲገሉና ሲደፍሩ በቸልታ መመልከቱ በቂ የወዳጅነት ስጦታ መስሎ አልተሰማውም። እናም ሸሪኮቹ የበለጠ እንዲደሰቱና ከእስከዛሬ በበለጠ ገንዘብ እንዲደጉሙት ለማበረታታት አዲስ አበባ በሚገኘው ኤምባሲያቸው ፊት ለፊት ኢትዮጵያንን ደበደበላቸው።

ወያኔ ከሳውዲ ጋር ያለው ግኑኝነት “የቢዝነስ ሸርክና” ነው። ቢዝነሱም ኢትዮጵያዊያንን በቁማቸው መሸጥንም ያጠቃልላል። የወያኔ ሹማምንት እና የሳውዲም ቱጃሮች በዘመናዊ ባርነት ንግድ ውስጥ አቀባይና ተቀባይ ናቸው። ለዚህም ነው እየተነገደበት ያለው ምስኪን ኢትዮጵያዊ እጣ ፈንታ በአዲስ አበባና በሪያድ አንድ ዓይነት የሆነው። እዛ ዱላ፤ እዚህም ዱላ። እዛ እስር፤ እዚህም እስር። እዚያ ስድብ፤ እዚህም ስድብ። እዚያ ቶርቸር፤ እዚህም ቶርቸር። በባርያ ንግድ ውስጥ አቀባዩም ተቀባዩም ባርያዉን መግዛታቸው፣ መስበራቸው፣ መግደላቸው የማይቀር መሆኑ የታወቀ ነው።

ሌላው አሳዛኝ ጉዳይ ደግሞ የወያኔ ድኩማን ሹማምንት የሚሰጡት አስተያየት መስማት ነው። በሳውዲ ለሚገኙ ኢትዮጵያዊያን ፍትህ ለመጠየቅ በመላው ዓለም እና በአዲስ አበባ ደግሞ በሰማያዊ ፓርቲ አስተባባሪነት ወደ ጎዳና በወጡ ኢትዮጵያዊያን የኮሚኒኬሽን ሚኒስትር ተብየው “የፋሺሽት መፈክር አንግቦ በተነሳቀሉ ዜጎች ስም የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት መጣር ብሎም መንግሥት በዜጎቹ ግዴለሽ እንደሆነ አስመስሎ ማቅረብ” ሲል ተሳልቋል።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ተብየው ጨምሮ ሁሉም የወያኔ ሹማምንት “ሳውዲዎች በግዛታቸው ውስጥ ያሻቸውን የማድረግ “ሉዓላዊ” መብት አላቸው፤ መንግሥታችን የሳውዲ አረቢያን ሉዓላዊ መብት ያከብራል” እያሉ ይከራከራሉ። ለመሆኑ ይህንን የሚሉት ከልባቸው ነው? ፈጽሞ። ኢትዮጵያዊያንን ማሰቃየትና መግደል የቢዝነሳቸው አካል ስለሆነ ነው እንጂ የሉዓላዊነት ትርጉም ይህን ያህል ተምታቶባቸው አይደለም።

ሰብዓዊ መብቶች አገር፣ ድንበር፣ ዜግነት፣ ወይም ሌላ ማናቸው ሰው ሠራሽ ህግጋት ሊጥሷቸው እንደማይገቡ የወያኔ ሹማምንት ቢያንስ ሲነገር ሰምተው ያውቃሉ። ማንኛውም ሰው ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ መገደል፤ ሰቆቃ (ቶርቸር) እንዲደርስበት ማድረግ፤ ጾታዊ ጥቃት እንዲደርስበት ማድረግ እንደማይቻል ሰምተው ያውቃሉ። ሰብዓዊ መብቶች ሰዎች ሰው በመሆናቸው ብቻ ሊያገኙት የሚገባ ክብር መሆኑ በተሳተፉባቸው በርካታ ዎርክ ሾፖች ሰምተዋል። ያም ሆኖ ግን በዘመናዊው ዓለም እንስሳ እንኳን ያገኘውን ክብር ኢትዮጵያዊያን ተነፍገው በሪያድ ጎዳናዎች ሲታረዱ፤ በጭካኔ ሲደበደቡና ሲገረፉ፤ ሴቶች ሲደፈሩ፤ ሕፃናት በረሀብና በእርዛት ሲቀጡ የወያኔ ባለሥልጣኖች የበዳዮች አፈቀላጤ ሆነው የሚከራከሩት በዳዮቹ ሸሪኮቻቸው ስለሆኑ ነው።

ይህ ድርጊት በወያኔ እየደረሰብን ያለው በደል ምን ያህል ሥር የሰደደ እንደሆነ እና የኢትዮጵያዊያን ሰቆቃ ምንጭ የት እንዳለ አመላካች ሆኗል።

“ትግላችን የነፃነት ትግል ነው” ስንል “ከማን ነፃ ለመውጣት?” እያሉ የሚሳለቁ እንደነበሩና እንዳሉም ይታወቃል። በወያኔ አገዛዝ ኢትዮጵያዊያን ወደ ባርነት ማሽቆልቆላቸው ይህ ተጨባጭ ማስረጃ ነው። ከወያኔ የባርነት አገዛዝ ነፃ እስካልወጣን ድረስ ሌሎች አገሮች መብቶቻችን የሚያከብሩልን በየአገራቱ ልምድ እና ከወያኔ ጋር ባላቸው ሽርክና መጠን ነው።

ለሳውዲ መንግሥትና ቱጃሮቹ ከነዳጅ ቀጥሎ የሀብታቸው ምንጭ ከየአገሩ የሚመጣላቸው የድሀ ጉልበት ነው። የሳውዲ ቱጃሮች ድሆችን ከባርነት ባልተሻለ መንገድ ረግጠው በመግዛት ኑሮዓቸውን ያደለቡ ናቸው። ለወያኔ አገዛዝ ደግሞ ከቡና ቀጥሎ ከፍተኛው የገቢ ምንጩ ዜጎቹን በመሸጥ የሚሰበስበው ነው። ለወያኔ፣ ኢትዮጵያዊያን ወንዶችና ሴቶች ትርፍ አምጪ ሸቀጦች ናቸው። ወያኔና ሳውዲ - ሻጭና ገዢ ናቸው።

ባርያ ከሻጩ ነፃ ሳይወጣ ከአንድ ገዢ ነፃ ቢወጣ ሌላ ገዢ ስለሚመጣ ዘለቄታነት የለውም። እኛም ከወያኔ ነፃ ሳንወጣ ከሳውዲ ነፃ መወጣት አይቻለንም፤ ቢቻልም ነፃነታችን ዘላቂነት አይኖረውም።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ በሳዉዲ አረቢያ በሚገኙ ወገኖቻችን ላይ በሚደርሰው ጥቃት ክፉኛ ተቆጥቷል። በዚህ የመከራና ጭንቅ ሰዓት ለወገኖቻችን ለመድረስ የሚቻለውን ጥረት ሁሉ ማድረግ እንዳለብን ያምናል። አባላቱ በነብስ አድን ርብርብ በግንባር ቀደምትነት እንዲሳተፉ መመሪያ አስተላልፏል። ይህ አጣዳፊ ሆኖም ጊዜዓዊ መፍትሔ ነው። በግንቦት 7 እምነት የችግሮቻችን ሰንኮፍ ያለው አዲስ አበባ ነው። ሰንኮፉን ሳንነቅል የሚደርስብንን ውርደት በዘላቂነት መቀልበስ አንችልም። ስለሆነም በችግር ላይ የወደቁትን ወገኖቻችን እየረዳን፤ የችግሮቻችን ምንጭ በሆነው ወያኔ ላይ የተባበረ ክንዳችንን እናንሳ ይላል።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ !!!**

---

## ፋሽስት ወያኔ በጅዳ የሚገኘውን ቆንስላ ጽ/ቤቱን

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

የኢትዮጵያን ሕዝብም ሆነ ባሁኑ ሰአት በሳውዲ አረቢያ ጥቃት እየደረሰበት ያለውን ወገናችንን ጥቅም እስካስገኘላቸው ድረስ ብቻ ነው ወገኔ የሚሉት ካልሆነ ግን ለምንም ደንታ የላቸውም” ይላሉ።

ፋሽስት ወያኔ ለአባይ ግድብ ቦንድ ሽያጭና የግዳጅ መዋጮ ወቅት በሳውዲ አረቢያም ሆነ በአጎራባች ሀገሮች እየተዟዟረ ከነዚህ ዛሬ ችግር ላይ ከሚገኙ ወገኖቻችን በተደጋጋሚ ገንዘብ መሰብሰቡ ሲታወስ፤ እውነትም ፋሽስት ወያኔ ዜጋ የሚለን ገንዘብ እስካለንና እስከደጎምነው ድረስ ብቻ መሆኑን ያረጋግጣል የሚሉ ጥቂቶች አይደሉም። ፋሽስት ወያኔ ጥቃት አድራሹን የሳውዲ መንግስት ለማውገዝ ድፍረት ማጣቱ ብቻም ሳይሆን ድርጊቱን ተቃውመው በአዲስ አበባ በሳውዲ ኢንባሲ ፊት ለፊት ሰልፍ የወጡ ወገኖቻችንን በቆመት እየቀጠቀጡ ማባረራቸውና ጥቂት የማይባሉትንም ማሰራቸው በሳውዲ ለሚገኙ ወገኖቻችን መከራና ግድያ ከሳውዲ መንግስት ገር ተስማምተዋል የሚሉ ወገኖችን አበራክቷል።

## የፌደራል ፖሊሶች ሳዑዲ አረቢያ ኤምባሲ ፊት ለፊት

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

እስር ቤት ውስጥ ሆኖ በድብቅ በስልክ እንደተናገረው የድርጅቱን ሊቀመንበር ኢንጂነር ይልቃል ጌትነትንና ምክትላቸው አቶ ስለሺ ፈይሳን ጨምሮ 15 አመራሮች ጃንሜዳ በሚገኝ እስር ቤት ውስጥ ይገኛሉ። ወጣት ጥላየ ታረቀኝ ታስሮና ድብደባ ተፈጽሞበት ከተለቀቁት መካከል አንዱ ሲሆን ፣ የወያኔን አገዛዝን ድርጊት ለመግለጽ እንደሚቸገር ገልጿል። ሰማያዊ ፓርቲ ከጥቃቱ በሁዋላ ባወጣው መግለጫ” የኢትዮጵያ መንግስት ከሳውዲ አረቢያ መንግስት ጎን በመቆም ዋና ተባባሪ መሆኑን በዛሬው እለት አስመስክሯል ብሎአል።

የግንቦት ሰባት ድምጽ ዘጋቢዎች ያናገሯቸዉ ብዙ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች የወያኔ ፖሊሶች የራሳቸውን ዜጋ በመደብደብና በማሰቃየት ብሎም በማሰር በሳውዲ በሚገኙ ኢትዮጵያዊ ወገኖች ላይ የተፈጸመውን በደል ሀገር ውስጥ በሚገኙ ንጹሀን ወገኖቻቸው መድገማቸዉ እጅግ በጣም የሚያሳዝን ነዉ ካሉ በኋላ በውሸት ዲሞክራሲ ስም የተደበቀው አምባገን አገዛዝ ህዝብን ለማሸማቀቅ የወሰደውን እርምጃ በመቋቋም አያት ቅድመ አያቶቻችን የሰጡንን አደራ በመቀበል ክብአችንንና ማንነታችንን በትግላችን እንደገና እናስከብራለን ብለዋል። የወያኔዉ ቃል አቀባይ ሽመልስ ከማል ለአልጀዚራ ቴሌቪዥን በሰጠዉ ቃለመጠይቅ ሰልፈኞቹ የተከለከሉት ባልተፈቀደ ሰልፍ ላይ በመገኘታቸውና ኢትዮጵያን ህዝብ በጸረ-አረብ ስሜት በማነሳሳታቸው ነው በማለት የተለመደዉን የቅጥፈት ንግግር ለአለም ህዝብ በማሰማት ለዜጎች ሳይሆን ለሳዑዲ ቱጃሮች ያለዉን ታማኝነትበግልጽ አሳይቷል።

---

# ወቅታዊ ችግሮቻችን የራሳችን መንግሥት ባለቤቶች እንድንሆን ይበልጥ ሊያበረቱን ይገባል!

በወያኔ አረመኔያዊ አገዛዝ ሳቢያ ከሀገራቸውና ከትውልድ ቀያቸው ተፈናቅለው በዐረቡ ዓለም በተለይም በሳዑዲ ዐረቢያ በሚገኙ ዜጎቻችን ላይ ሰሞኑን እየደረሰ የሚገኘውን ዘግናኝ ሰቆቃና ግድያ በመሪር ስሜትና በንቃት እየተከታልን ነው። አበው "ባለቤቱ ያቀለለውን አሞሌ ባለዕዳው አይቀበለውም" እንዲሉ እነዚህ ወገኖቻችን በዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ዘንድ ‹የሀገራቸው መንግሥት ነው› የሚባልለት የወያኔው መንግሥት እንኳንስ በባዕድ ሀገር በሚገዛው ሀገርም ውስጥ የሚያካሂደውን የሙብት ገፈፋና ሕዝቤ በሚለው ዜጋ ላይ በዘር እየከፋፈለ የሚያራምደውን የግፍ አገዛዝ ዐረቦቹም ሆኑ ቀሪው ዓለም ያውቁታል። በመሆኑም ለነዚህ ምሥኪን ዜጎች የሚጮኽላቸውም ሆነ ለሙብታቸው መከበር የሚቆረቆርላቸው አንድም መንግሥታዊ አካል እንደሌለ ከበፊት የተገነዘቡት እውነታ ነው። በወገኖቻችን ላይ ይህን ሁሉ ሰማይና ምድር የማይችሉት የግፍ ቁልል እነዚህ የዐረብ መንግሥታት የፀጥታ ኃይሎች ሲከምሩባቸው ማንም ዝምባቸውን እሽ የሚል ወይም ጠንከር ባሉ ቃላት እንኳን ተቃውሞ የሚያቀርብ አካል እንደማይር ያውቃሉ። ለዚህም ነው ታላላቅ የሚዲያ አውታሮች ሳይቀሩ ሀገሪቷንና ሕዝን በመናቅ በዝምታቸው መግፋትን የወደዱት። ይህ ነገር ከሃይማኖትም ይሁን ከቀለም፣ ከዘርና ከፖለቲካዊ እሳቤዎች አኳያ የሰው ልጅ ተፈጥሮን ባሕርይና የሀገራትንና የመንግሥታትን ተጻራሪ ድርብ አቋሞችን ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ነው። "ሰው ለሰው የሚጨነቀው፣ ምን ዓይነት ሰው ሲጎዳ ወይም ምን ዓይነት ሕዝብና የትኛው ሀገር ችግር ላይ ሲወድቅ/ሲወድቁ ይሆን?" በሚል ከፍተኛ ፍልስፍና ውስጥ የሚያስባ ልዩ አጋጣሚ ፈጥሯል። በእውኑ ኢትዮጵያና የኢትዮጵያ ሕዝብ በበለፀጉ ሀገሮች የአንድ ንጉሥ-ንግሥት ንብረት ከሆነች ውሻ ያንሳሉን? ንግሥት ኤልሣቤጥ የሚወዷት የቤት ድመት ወይም የንጉሥ አብደላ የቤተ መንግሥት ውሻ ቢሞቱ ሲኤንኤንንና ቢቢሲን የመሳሰሉ ላለው የሚያሽቃብጡ ዓለም አቀፍ የዜና ተቋማት የመክፈቻ ዜናቸው እንደሚያደርጓቸው አይጠረጠርም። ወትሮም ብሂሉ "ላለው ይጨመርለታል" ነውና። እንደዚህ ያለው አካሄድ በውነቱ ቅስምን የሚሰብርና ከ21ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ሰለጠነ የሚባል ማኅበረሰብ የሚጠበቅ አልነበረም።

በኢትዮጵያውያን ስደተኞች ላይ እየተደረገ ያለው ሰቅጣጭ የሕይወት ገጠመኝ በሌሎች ሀገራት ሕዝቦች ላይ ቢደረግ ኖሮ በአሁኑ ወቅት ዓለማችን ከዳር እዳር በተቃወሰች ነበር። በዚህ ዘመን እንደኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን የተዋረደ የለም፤ ለዚህ ያበቃንም ይበልጡን በየምንሄድባቸው አካባቢዎች ያሉ መንግሥታት ብቻ ሳይሆኑ እቤታችን ያለው እሾህ፣ እዚያው ኢትዮጵያችን ውስጥ በአራት ኪሎ ቤተ መንግሥት የመሸገውና በመላዋ ሀገራችን እንደመዥገር የተጣበቀው ወያኔ ነው። ስለዚህ ዋናው ጠላታችን ቤታችን ውስጥ ሁሉንም ነገር ተቆጣጥሮ ለመከራና እንግልት የዳረገን ወያኔ እንጂ ከዚህ ክፉ አውሬ የጭራቆች ቡድን ቀድሞ በኃላፊነት የሚጠየቅ ሊኖር አይገባም። እርግጥ ነው - በችግራቸው ጊዜ በጥሩ እንግዳ ተቀባይነት ከደረስንላቸው ወገኖች ይህን መሰል ግፍና ስቃይ ማየትና መስማት ዕንቆቅልሽ መሆኑ አይቀርም።

የአንድ ሀገር ዜጎች በተለያዩ ምክንያቶች በፍቅርም ይሁን በጠብ፣ በሥራና ለሥራም ይሁን በስደትና በጦር ምርኮኝነት ከሀገራቸው ወጥተው በሌሎች ግዛቶች የሚገኙበት ሁኔታ በተለይ በዚህ ዘመን በስፋት ይስተዋላል። በዚህን ጊዜ ባሉን ዓለም አቀፍ ሕግጋት መሠረት የዜጎች እንቅስቀሰሴና ዝውውር የዲፕሎማሲን መስመር በጠበቀ ሁኔታ ይከናወናል እንጂ እንዲህ እንደሰሞኑ አንዱ በሌላው ላይ ኢሰብአዊ ድርጊትን አይፈጽምም። "በዚህን ጊዜ ውስጥ ሀገራችንን ለቃችሁ ውጡ፤ ካልወጣችሁ እንዲህና እንዲህ የመሰለ ችግር ይደርስባችኋል" ተብሎ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል እንጂ ድንገት ከመሬት ተነስቶ የሌሎች ሀገራት ዜጎችን ላልተጠበቀ ኢሰብአዊ ድርጊት ማጋለጥ ሰብአዊም ሃይማኖታዊም መደላድል የሌለው ዐይን ያወጣ ወንጀል ነው።

የአሁኑን የኢትዮጵያ መንግሥት ተብዬውን ዓይነት ሳይሆን ሁነኛ የሕዝብ አገልጋይ መንግሥታት ባሉባቸው ሀገራት ውስጥ ብዙ አስገራሚ ግን ተገቢና የሚጠበቅ መንግሥታዊ ፈጥኖ ደራሽነትንና ከአደጋ ታዳጊነትን ማየታችን በጣም የተለመደ ነው። ብዙ አብነቶችን መጥቀስ ቢቻልም የቅርብ ጊዜውን የሻሊትን ጉዳይ ብቻ ማውሳት በቂ ነው።

ሻሊት እሥራኤላዊ ወጣት ወታደር ነበር። ቀደም ሲል በሀገራዊ ግዳጅ ላይ እያለ በፍልስጥኤማውያን ይያዝና ሥውር ቦታ ይታሰራል። በሁለቱ ወገኖች መካከል ብዙ ጊዜ የወሰደ ድርድር ይካሄዳል። የአንድ ዜጋ ጉዳይ መላ እሥራኤላውያንን ማወዛገቡን ይቀጥላል። በመጨረሻም ከአንድ ሺህ በላይ እሥረኛ በአንድ ሻሊት አስፈትተው ፍልስጥኤሞች ይህን ወጣት ወታደር ይለቁታል። ለሀገርና ለሕዝብ ተቆርቋሪ መንግሥት ማለት እንደዚህ ነው። እሥራኤል ሕይወት ያለውን ዜጋዋን ብቻም ሣይሆን ለአንድ በጦርነት ለተሰዋና በጠላት ቁጥጥር ሥር የሚገኝ በድን ዜጋዋ ሕይወት ባላቸው በርካታ ምርኮኞች የምትለውጥ ለዜጎቿ ስሱ የሆነች ሀገር መሆንዋን ከበፊትም የምናውቀው ነው። በዘመናችን ዲፕሎማሲያዊ ጥረት በማድረግ ለዜጎች ሙብት መከበር ከመታገል አንጻር ሣይሆን በየትም ሥፍራ የሚኖሩ ዜጎች ለሀገር ውርደትና ለአጠቃላዩ የሕዝቡ ጎልውና ማክተም ሌት ከቀን ተግቶ በመሥራት አኳያ ከወያኔ መንግሥት ሌላ በዓለም ሌላ ሀገር ሊኖር እንደማይችል በልበ ሙሉነት መወራረድ ይቻላል። እኛ ላይ እሳት ነው የጣለብን።

"ጽድቁ ቀርቶብኝ በቅጡ በኮነነኝ" እንዲሉ እኛ ኢትዮጵያውያን እንደእሥራኤል ያለ ለዜጋው እንስፍስፍ መንግሥት ማግኘቱ ቀርቶብን በዚህን ዓይነት አደጋ የበዛበት ወቅት የዜጎቹ ደኅንነት ካልተጠበ የዲፕሎማሲና የንግድ ግንኙነቶቹን እንደሚያቋርጥ ለማስመሰልም ቢሆን በማስፈራራት ለጨፍጫፊው መንግሥትና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ዓለም አቀፍ ተቋማት አቤት የሚል መንግሥት ቢኖረን ምንኛ በታደልን ነበር። ወያኔ ግን ተፈጥሮው እንደነዛው እንደጨፍጫፊዎቹ በመሆኑ እዚህ ግባ የሚባል ውኃ የማያነሣ ሰበብ በመስጠት ዜጎች እየተጨፈጨፉ ባሉበት ሁኔታ ሚዲያዎቹ ሁሉ በአሸሸገዳሜ ዘፈን ተሞልተው በሀገር ሰላም የተለመደ የማደንቆሪያ ልማታዊ ተብዬ ፕሮፓጋንዳውን በስፋት ቀጥሎበት ይታያል። ይህም በጣም ያሳዝናል።

ወያኔ ራሱ ህጋዊ መንግሥት የሆነ ይመስል ከሀገር የሚሰደዱ ዜጎችን ከህግ መስመር ውጪ ነው የወጡትና አያገባኝም በሚል ማደናገሪያ ከመንግሥታዊ ኃላፊነቱ እየሸሸ ነው። በመሠረቱ ቀድሞ መምጣት ያለበት ዜግነት እንጂ ሕግ አይደለም። ሰው የሠራው ሕግ በተፈጥሮ ከተገኘ ሰው መቅደም የለበትም። እንኳንስ ለዜጎቹ ምንም ነገር ካላሟላ ጨቋኝ መንግሥት ይቅርና ሁሉም ነገር ከተመቻቸላቸው ያደጉ ሀገሮችም ሳይቀር ከመንግሥታቸው በመቃረን ጭምር ሰዎች በተለያዩ ምክንያት ከሀገራቸው ይወጣሉ። ለምሳሌ ስኖውደን የተባለው አሜሪካዊ በቅርቡ ከሀገሩ ሸፍቶ በራሽያ ውስጥ ይገኛል። በዚህ ሰው ላይ ማንም አካል ተነስቶ ኢሰብአዊ ድርጊት ቢፈጽምበት የአሜሪካ መንግሥት ራሱ እንደተዋረደ ይቆጥሩታልና ያ ስኖውደንን የሚያንገላታ አካል የዚህችን ልዕለ ኃያል የሆነች ሀገር ጡንቻ ይቀምሳል እንጂ "ከእኛ ጋር ተጣልቶና አስቀይሞን ስለወጣ እንኳን የእጁን አገኘ!" ከሚል የመሠሪዎች ቂም በቀለኝነት በመነሣት አሜሪካውያኑ እጃቸውን አጣጥፈው አይቀመጡም። ወያኔ ግን ተፈጥሮው በቂምና በበቀል የታጀለ በመሆኑ የሣዑዲን መንግሥት እንዲያውም በባለውለታነት እስካሁን ከሰጣቸው ሰፋፊ እርሻዎች በተጨማሪ ሌላ ትላልቅ መሬቶችን በሽልማት ሳይሰጣቸው አይቀርም። ይህ መንግሥት በሀገር ውስጥም በሰው ግዛትም እየገባ ዜጎቹን የሚጨፈጭፍ በመሆኑ ለዜጎች የሚቆረቆር ተፈጥሮ በጭራሽ የለውም። መባጽዮን ጃተኒን በሰላም በተቀመጠበት ኬንያ ውስጥ ቅጥረኛ ነፍሰ ገዳዮቹን አሰማርቶ ያሰገደለ ወያኔ ለዜጎች ይቆረቆራል ብሎ ማሰብ የዋህነት ነው። ሰሞኑንም የግንቦት ሰባትን ሕዝባዊ ኃይል አመራር ለማስገደል እበላ ባይ ወንጀለኞችን አሰርጎ ከፍተኛ የነፍስ ማጥፋት ወንጀል ሙከራ ያደረገ የባለጌዎች መንግሥት ራሱ ገፍቶ ያወጣቸውን ዜጎች ደኅንነት ለማስጠበቅ ከወዳጆቹና ከዓላማው አራማጆች የዐረብ መንግሥታት ጋር ይቀያየማል ብሎ ማሰብ ዘበት ነው። ለሕዝብና ለሀገር ውርደትና አጠቃላይ የሞራልም ሆነ የማኅበራዊ ዕሤቶች ውድቀት የቆመን አካል ደግ ነገር እንዲያደርግ መጠበቅ የወያኔን ሥረ መሠረትና የተፈጥሮ ባሕርይ በቅጡ አለመገንዘብ ነው። መፍትሔው ግን በያንዳንዳችን እጅ ውስጥ ነው።

እንደግንቦት ሰባት ያለው አማራጭ አንድና አንድ ብቻ ነው። ይሄውም ይህን የዜገች ፀር የሆነ የወንበዴ መንግሥት በሁሉም ሥልቶች ተረባርቦ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ማስወገድ ነው። ይህ ሲሆን ነው ዜጎቻችን በሚሄዱበት ቦታ ሁሉ አንገታቸውን ቀና አድርገው እንዲሄዱ የሚያስችላቸውን የኔ ነው የሚሉት ሕዝባዊና ዴሞክራሲያዊ መንግሥት ማቆም የሚቻለው። ያኔ ነው ኢትዮጵያ ከተቀበረችበት ተነስታ በዜጎቿ የጋራ ምክክርና ስምምነት በአዲስ ጠንካራ መሠረት ላይ የሚገነባ ሁሉንም እኩል የሚያይ፤ ለሁሉም እኩል መኩሪያ የሚሆን መንግሥት ሊመሠረት የሚችለው። ያኔ ነው የሀገራችንን የሰውና የተፈጥሮ ሀብት ለሀገራችን በማዋል ድህነትንና ስደትን በተባበረ ክንዳችን የምንገታው። ያኔ ነው ሀብታችን በግለሰቦች እየተመዘበረ ለጥቂቶች መንደላቀቂያ መሆኑ የሚቀረውና ለሕዝቡና ለሀገሪቱ ዕድገት የሚውለው። ያኔ ነው በዓለም የተበተነው የተማረ የሰው ኃይላችንና በብዙ ዕውቀትና የሕይወት ልምድ የዳበረው ዜጋችን ወደ ሀገሩ መጥቶ ሀገር ቤት ካለው ኃይል ጋር በመተባበር ኢትዮጵያችንን ከገባችበት አረንቋ የሚያወጣትና ትንሣኤዋም በአዲስ መልክ የሚታወጀው። ለዚህ ሁሉ ተጨባጭ ምኞት እውንነት ደግሞ ሁላችን እጅ ለእጅ ተያይዘን ይህን የበሰበሰና የፈራረሰ ግን በቅርጹ ሲታይ ሕይወት ያለው የሚመስል የወሮበሎች መንግሥት በጋራ ትግል ከነሰንኮፉ ፈንቅለን ልንጥለው ይገባል። ዋናው የችግራችን ሁሉ መባቀያ አዲስ አበባ ላይ ቁጭ ብሎ መንስኤውን ትተን በውጤቶች ላይ ብቻ ማዘኑና መቆዘሙ እንዲሁም ባልተቋረጠ የሀዘን ድባብ ውስጥ ተቀምጦ ማንባቱ ዋጋ የለውም። የኛን ሥራ ወደጎን ትተን ወያኔ በሚፈጥራቸው አፍራሽ ተግባራትና ውጤታቸው ዝንትዓለሙን ማላዘኑ የነሱን ዕድሜ ከማራዘም ውጪ ለኛ የሚተርፍ አወንታዊ ፋይዳ የለውም። ከተባበርን የዚህ መንግሥት ዕድሜ ከሣምንታት አይረዝምም፤ ካልተባበርንና አንዳችን የአንዳችንን ጉድጓድ በመቆፈር ተግባር ከተጠመድን ወያኔ በጀመረው መንገድ ቀጥሎ ሀገራችን በለዬለት ሁኔታ ከዓለም ካርታ እንድትሰረዝ ፈቃደኞች ሆነናል ማለት ነው። ምርጫው የኛው ነው።

በመጨረሻም በሰሞኑ የወገኖቻችን ዕልቂት ምክንያት በቀጥታም ይሁን በተዘዋሪ የወያኔው ግፈኛ አገዛዝ ሰለባ የሆኑ ወገኖቻችንን ነፍስ ይማር እንላለን፤ ለቤተሰቦቻቸው እንዲሁም ውርደቱና ታሪካዊ አንድምታው አሉታዊ ጥላውን ለሚያሳርፍበት ለመላው ሕዝባችንም መጽናናትን እንመኛለን።

## የስዊድን የጦር ፍርድ-ቤት አቃቤ ህግ በወያኔ ባለስልጣናት ላይ ምርመራ እንዲካሄድ ወሰነ

የሲዉዲን የጦር ፍርድ ቤት አቃቤ ህግ ዘረኞቹ የወያኔ መሪዎች በኦጋዴን ህዝብ ላይ ያደረሱትን ግፍ፤ በደልና ሰቆቃ አስመልክቶ ጉዳዩ በሚመለከታቸዉ ዋና ዋና የወያኔ ባለስልጣኖች ላይ ምርመራ እንዲካሄድ መወሰኑን ከሲዉዲኗ መዲና ስቶክልሆም የሚደርሱን ዜናዎች አስረዱ። ፍርድ ቤቱ እዚህ ውሳኔ ላይ የደረሰው በቅርቡ በኦጋዴን የተፈጸመውን የሰብአዊ መብት ጥሰት በተመለከተ፣ የክልሉ የወጣቶች ማህበር ሊቀመንበርና የፕሬዚዳንቱ የግል ድረገጽ ማኔጀርና አማካሪ የነበረው ወጣት አብዱላሂ ሁሴን በኦጋዴን የጦር ወንጀልና የሰብአዊ መብቶች ጥሰት መፈጸሙን የሚያሳይ ማረጃ ለፍርድ ቤቱ አቃቤ ህግ ማቅረቡን ተከትሎ ነው። የጦር ፍርድ ቤቱ ዋና አቃቤ ህግ ክሪስተር ፒተርሰን በ10 የኦጋዴን ክልል ባለስልጣናትና የመከላከያ አዛዦች ላይ የቅድመ መርምራ እንዲካሄድ የወሰኑ ሲሆን ከተመርማሪዎች መካከል የክልሉ ፕሬዚዳንት አብዲ ሙህመድ ኡመርና ምክትሉ አብዱላሂ ዌረር እንደሚገኙበት ወጣት አብዱላሂ ከኢሳት ጋር ባደረገው ቃለምልልስ ገልጿል።

ውሳኔው ለኢትዮጵያውያን ከፍተኛ ድል ነው ያለው አብዱላሂ፣ ምርመራ መጀመሩንም ገልጿል። ምርመራው እንደተጠናቀቀ ሁለት አማራጮች ሊኖሩ እንደሚችል ተናግሯል። አንደኛው አማራጭ ጉዳዩን በስዊድን የጦር ፍርድ ቤት ማየት ሲሆን፣ ሌላው ደግሞ ወደ አለማቀፉ የወንጀል ፍርድቤት መላክ ነው። በመላው አለም የሚገኙ ኢትዮጵያውያን መረጃዎችን በመላክ እንዲሁም የምስክርነት ቃላቸውን በመስጠት እንዲተባበሩ ወጣት አብዲ ገልጿል። ከዚህ በተጨማሪ

በተለያዩ የአለም ክፍሎች የሚገኙና በወያኔ አገዛዝ በደል የደረሰባቸው ሰዎች መረጃዎቻቸውንና እንዲሁም የምስክርነት ቃል ለመስጠት የሚፈልጉ ሁሉ የስልክ ቁጥራቸውን በ0031 68 71 54 530 እየደወሉ ወይም በ editor@ethsat.com ቢልኩ ኢሳት ጉዳዩን በቅርብ ከሚከታተሉ ወገኖች ጋር የሚያገናኛቸው መሆኑን የኢሳት ዝግጅት ክፍል አስታውቋል።

## ባርነትን ከሚያላምደን የተቃዉሞ ትግል የመላቀቅ ግዜዉ አሁን ነዉ !

የኢትዮጵያ ህዝብ ከወያኔ አገዛዝ ጋር የሚያደርገዉን ትግል በአሸናፊነት ለመወጣት መዉሰድ ካለባቸዉ ዋና ዋና እርምጃዎች ዉስጥ አንዱና ዋነኛዉ ሁሌ ወደኋላ ከሚጎትተንና ባርነትን ከሚያላምደን የተቃዉሞ ሰልፍ መላቀቅ ነዉ ሲል አለም አቀፉ የኢትዮጵያ ሴቶች ድርጅት ከሰሞኑ አንድ መግለጫ አወጣ። ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ሴቶች ድርጅት፣ ሰሞኑን በወገኖቻችን ላይ በደረሰው እና እየደረሰ ባለው ጥቃት ጥልቅ ሃዘን እና ቁጭት እንደተሰማዉ ገልጾ የዛሬው ልዩ ጥሪያያችን ለመከራችን ምንጭና መነሻ የሆነውን የትግሬ ነፃ አውጭ ግንባር ከስልጣን ማስወገድ ዋናና ቀዳሚ የመፍትሄ ተግባራችን ሊሆን እንደሚገባ አሳስቧል። ድርጅቱ በመግለጫዉ ላይ እኛ ኢትዮጵያውያን አገራችንን እና ወገናችን የምንወድ ሩህሩህ እና አዛኝ ሕዝብ ነን። በወገን ላይ መከራና ስቃይ፣ ግፍና ሞት ሲደርስበት በጣም እናዝናለን ፣እናለቅሳለን፣ ሆኖም ግን የዚህ ዓይነቱ ችግር እና ሰቆቃ እንዳይደርስብን ተገቢውን ንቃትና ጥንቃቄ አናደርግም፤ ግፍና መከራም በሚከስትበትም ግዜ በአስቸኳይ መከራውን የሚያስቆም ቆራጥ እርምጃ አንወስድም። ይህ አንዱ አሳሳቢና መቀየር ያለበት ነባራዊ ዕውነታ ነው። ለዚህም ነው ለዘመናዊው ቀስ በቀስ ባርነትንና የበታችነትን ከሚያላምደን የተኮላሸ የተቃውሞ የትግል ስልት እንላቀቅ የምንለው::

እስከዛሬ ሰልፍ ወጥተናል ፣መግለጫ የያዙ ደብዳቤዎች ጽፈናል፣ ይመለከታቸዋል ላልናቸው የዓለም መንግስታት እና ዓለማቀፋዊ ተቋማት አቤት ብለን አመልክተናል ፣በአንጻሩ የኢትዮጵያውያን መከራና ሰቆቃ እንዲሁም ብሔራዊ ውርደት እየጨመረ መጣ እንጂ መፍትሄ አልሆነንም። ወገኖቻችን በገሃድ በየአደባባይ ይደፈራሉ ይቀጠቀጣሉ፣እየታፈኑ ወዳልታወቀ ሥፍራ ይወሰዳሉ፣ ይታረዳሉ፤ አቤት ባይ የራስ መንግስት የለንም፣ ዓለም አቀፍ ተቋማት፣ የሰብዓዊ መብት ተከራካሪ ነን ባይ ድርጅቶች እንዲሁም ዓለም አቀፍ የዜና አውታሮች፣ ሁሉም አንድ ላይ ያደሙ ይመስላል፣ አላየንም አልሰማንምን መርጠዋል፤ ይህ ለእንኛ እንግዳ ና አዲስ ሊሆን የሚገባ ጉዳይ አይደለም።

ስለዚህ ይህን መከራና ውርደት የሚያስቆም ለውጥ ለማምጣት ሁለት ነባራዊ ሁኔታዎች መቀየር አለባቸው። አንደኛው እስከዛሬ የተለመደውና የሚመቸንን መፍትሄ ቢስ የተቃውሞ ሂደትን መቀየር ሲሆን፣ ሁለተኛው እየተባባሰ የመጣውን የኢትዮጵያውያንን ስቃይና መከራ በፍጥነት ማስቆም ነው። ይህም ተልዕኮ የሚሳካው፣ የችግራችን ምንጭ የሆነውን ፣ ሕዝብን እና አገርን ለባርነት ገበያ አቅራቢውን ደላላ የትግሬ ነፃ አውጭ ግንባር በኃይል ስናስወግድ ብቻ ነው። ይህን በዋናነት ውጤታማ ለማድረግ የሚቻለውም የችግሩ ገፈት ቀማሽ የሆነው ኢትዮጵያዊ ኃይል ሲነሳ ብቻ ነው። ይህም የሚሳካው ኢትዮጵያውያን ለራሳቸው ነፍስና ሕይወት ዋጋና ክብር ሲሰጡ ነው።

## ሳኡዲ ዉስጥ የነበረዉ የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ገንዘብ በመለስ ዜናዊ ትዕዛዝ መወረሱ ተሰማ

ከደርግ ዘመን ጀምሮ ለረጂም ግዜ ሳዑዲ አረቢያ ዉስጥ የኖሩ ኢትዮጵያዉያን ለትምህርት ቤት ማሰሪያና ለተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮች ማስፈጽሚያ ይሆነናል በማለት ከግል ኪሳቸው እያወጡ ያጠራቀሙት ገንዘብ የቀድሞው ጠ/ሚ መለስ ዜናዊ በሰጠዉ ትእዛዝ ገንዘቡ ተወርሶ በሪያድ የሚገኘው የኢትዮጵያ ኢምባሲና የአምባሳደሩ መኖሪያ እንዲሁም ጅዳ የሚገኘው የቆንስላ ጽህፈት ቤት እንዲሰራበት የተደረገ መሆኑን ኢሳት ሬዲዮና ቴሌቪዥን አስተማማኝ ምንጮችን ጠቅሶ ዘገበ። ይህ በወቅቱ 50 ሚሊዮን ሪያል ወይም በጊዜው በነበረው ምንዛሬ ከ13.5 ሚሊዮን ዶላር በላይ ደርሶ የነበረዉ ገንዘብ የሳዑዲ ባለስልጣኖችን አይን ሊስብ ይችላል በሚል የኮሚኒቲው መሪዎች በኢትዮጵያ ኢምባሲ የባንክ ሂሳብ ዉስጥ እንዲቀመጥላቸውና ገንዘቡን ሲፈልጉ ከአምባሳደሩ ጋር በጋራ በመሆን ለማንቀሳቀስ ተስማምተዉ እንደነበርና ይህ ስምምት ያለ ምንም ችግር ለብዙ ግዜ እንደቆየ ይተወቃል።

ወያኔ/ኢህአዴግ ስልጣን እንደያዘ ገንዘቡን ለመጠቀም በመፈለጉ የኮሚኒቲ መሪዎችን በጥቅማጥቅም ለመደለል ዘመቻ ጀመረ። ለኮሚኒቲ መሪዎቹ አዲስ አበባ ውስጥ መሬት እንደሚሰጣቸውና ቤቶችን ሰርተው እንደሚኖሩ ፣ መንግስት መሪዎቹ ለሚያቀርቡት ጥያቄ አስፈላጊውን እገዛ እንደሚያደርግላቸውም ቃል ገባላቸዉ። ሆኖም የስደተኞቹ ተወካዮች ገንዘቡ የህዝብ በመሆኑና ለትምህርት ቤት ማሰሪያና እንዲሁም ለተለያዩ ችግሮች ማቃለያ የተቀመጠ ነዉ በሚል የወያኔን ጥያቄ አንቀበልም የሚል መልስ ሰጥተዋል። በጉዳዩ ላይ እጁን ያስገባዉ መለስ ዜናዊ ለአንዳንድ የኮሚኒቲው መሪዎች " መሬት እንኳ ባይኖር መስቀል አደባባይን ሸንሽኜ አከፋፍላችሁዋለሁ" በማለት ቃል እስከመግባት ደርሶ እንደነበር ለማወቅ ተችሏል። የኮሚኒቲ መሪዎች የመለስን ማባበያ ለመቀበል ፈቃደኛ አለመሆናቸው ሲታወቅ መለስ በረሃ ዉስጥ በለመደዉ አሰራር ገንዘቡ ለግንባታዎች እንዲውል ቀጥተኛ ትእዛዝ ሰጠ።

በዚህ የተበሳጩት የወቅቱ የኮሚኒቲው መሪ አቶ እርቁ ገዳ ጉዳዩን ወደ ፍርድ ቤት ለመውሰድ ቢፈልጉም፣ ኤምባሲው ግትር ናቸው ያላቸዉን አቶ እርቁን በሌላ የኢህአዴግ ደጋፊ እንዲተኩ በማስደረግ ክሱ እንዳይንቀሳቀስ አድርጓል።አንዳንድ የኮሚኒቲው መሪዎችም ምንም ማድረግ አለመቻላቸውን ሲያዩ ወደ አዲስ አበባ በመሄድ ቃል የተገባላቸው ቦታ እንዲሰጣቸው ጠይቀዋል። ይሁን እንጅ የጠየቁትን ቦታ ካለማግኘታቸውም በላይ አንዳንዶች መንግስት በጠየቃችሁ ጊዜ ግትር አቋም አሳይታችሁኋል በሚል የተለያዩ ችግሮች እንደደረሰባቸዉ ለማወቅ ተችሏል። ብዙ አስተያየት ሰጪዎችገንዘቡን የኢትዮጵያ መንግስት ባይጠቀምበት ኖሮ፣ በሺዎች የሚቆጠሩ በሳውዲ አረቢያ የሚገኙና ወደ ኢትዮጵያ የተመለሱ ሰዎችን ለመርዳት ሊውል ይችል እንደነበር አስተያየት ሰጥተዋል።ጉዳዩን በቅርቡ ከሚያውቁ ሰዎች ጠይቀን እንደተረዳነው በወቅቱ መንግስት የሳውዲ አረቢያን የኢትዮጵያ ኪሚኒቲ ገንዘብ ብቻ ሳይሆን የሌሎችንም የገልፍ አገሮች የኮሚኒቲ ገንዘቦችን በመውሰድ ለግንባታው አውሏል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ከሳውድ አረቢያ ወደ አገረቸዉ ኢትዮጵያ የሚመለሱ ኢትዮጵያውያንን ቁጥር በተመለከተ የወያኔ ባለስልጣኖች የሚሰጡት የተምታታና እርስ በርሱ የተጣረሰ መግለጫ ህዝቡን ጥርጣሬ ላይ እንደጣለዉ ከአገር ቤት የሚመጡ ዜናዎች አመለከቱ። እጅግ በጣም ዘግይቶ ችግር ላይ የወደቁ ኢትዮጵያዉያንን ከሳውድ አረቢያ ማስወጣት የጀመረው የወያኔ ዘገዛዝ፣ እስካሁን ድረስ የተመላሾችን አህዝ በተመለከተ የሚሰጠው መግለጫ ፍጹም ግራ የሚያጋባ ሆኗል። የውጭ ጉዳይ ሚኒስተሩ ዶ/ር ቴዎድሮስ አድህኖም በቲውተር ወደ አገር ቤት የተመለሱት ኢትዮጵያውያን ቁጥር 10 ሺ 707 ነው በማለት የገለጸ ሲሆን የቴዎድሮስ ቃል አቀባይ አምባሳደር ዲና ሙፍቲ ደግሞ የተመላሹን ቁጥር 4 ሺ 961 ነዉ በማለት ለጀርመን ራዲዮ ተናግረዋል። ቴዎድሮስ አድህኖምና አምባሳደር ዲና ሙፍቲ ሁለቱም የዉጭ ጉዳይ ሚኒስትር መሪና ቃል አቀባይ ሆነዉ በአንድ ቀን ዉስጥ እንዲህ የተዛባና ግራ የሚያጋባ መግለጫ መስጠታቸዉ የሚያሳየዉ ስራቸዉ ሁሉ የታሰበበትና ይህዝብን ችግር ለማቃለል ሳይሆን የግብር ይዉጣ ስራ መሆኑን ነዉ በማለት ህዝቡ መተቸት ጀምሯል።


**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

**መካከኛ ሞገድ**:- በ 358 MB, በ 837 kHz

**አጭር ሞገድ**:- በ 31 MB በ 9700 KHz

በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz

በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2፡30 እስከ 3፡00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 እስከ 3፡30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

ማሳሰቢያ:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።



**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org

## የሃያ ዓመት ደብዳቤ

**ከፈቃደ ሸዋቀና** (ክፍል 3 የመጨረሻ ክፍል)

አንድ ነገር ደሞ ልንገርሽ። ይህንን ሬናይሰንስ (ህዳሴ) ላይ ነሽ የሚሉሽን ሰዎች ተዉ በያቸው። መንገድና ግንብ መስራት መጥፎ አይደለም። ህዳሴ ግን ትርጉሙ ይህ አይደለም በያቸው እነዚህን ስልጣንና ዕውቀት የተምታታባቸውን ሰዎች። ህዳሴ የሚጀምረው ጭንቅላት ውስጥ መሆኑን ንገሪ። አብርሆተ ህሊናን፣ ሕግን፣ ሥነ ጥበብን፣ የህሊና ነጻነትን፣ የምርምር ፍንዳታንና በራስ መተማመንን ሌላም ብዙ ነገርና ሁለንተናዊ ትንሳኤን የሚያካትት ነገር ነው በያቸው። አትሸንገይ። እኔ ነገሩ የቀፈፈኝ ያባይን ድልድይ ጃፓኖች ሙሉ በሙሉ በራሳቸው ገንዘብ ሰርተው ካስረከቡን በኋላ “ህዳሴ ድልድይ” ተብሎ በጠቅላይ ሚንስትሩ ተሰየመ የተባለ ጊዜ ነው። ልመና ብዙ ገብዘብ ሊያስገኝ ይችላል። ህዳሴ ግን አያመጣም። ጽድቁ ቀርቶ በወጉ በኮነነሽ። በባዶ ቤት ወግ መጠረቅ ራት አይሆንም።

ሚቹ ገዢሽ አቶ መለስ አፈሩ ይቅለለውና ከሰራቸው ስራዎች ሁሉ አባይን ለመገደብ መነሳቱን እንደትልቅ ቁም ነገር አይቼለት ነበር። ሀሳቡ ካንድ የጎሳ ብሄርተኛ ይመጣል ብዬ አላሰብኩም ነበር። ውጥኑን ስሰማ ደብዳቤ ጽፌ አመሰግነዋለሁ ብዬ ነበር። ሕዳሴ የሚለውን ስያሜ ከፈለገ ግን ሌሎች ማድረግ ስላለበት ነገር ሳልነግረው ስለሞተ ይቆጨኛል። ምናልባት እሱ ከነገረን ነገር ውጭ ውልፍት ካልን እንኮነናለን ብለው ለሚፈሩ ደቀ መዛሙርቱ ነግሮልን ይሄድ ነበር። ይህን የሚያክል ፕሮጀክት በባዶ ኪስ ጀምሮ አብሮት የሚሄድ የፖለቲካ ጥበብና ፈቃደኝነት ከጎኑ ሳያስቀምጥ መቅረቱ ያለውን ችግር ልነግረው ፈልጌ ነበር። ልጆችሽ ምንም ብንወድሽ እንደ እንስሳ እየተነዳን፣ እንጨት እንጨት የሚል ፕሮፓጋንዳ እየጠጣንና እየተሰደብን የምንሰራው ነገር አለመሆኑን ምንም የዋህ ብትሆኚ የምታጭው አይመስለኝም። የድሆችሽን መቀነት በማስፈታት የምትሰበስቢው መዋጮ ቆሞ እዚህ የኔ ስደት ሀገር ያለነው ልጆችሽ ብቻ ያለን ቢያልቅብን በክሬዲት ካርድ ተበድረን እንሰራው ነበር ግድቡን። የምንሰራው ግን ለሰማይ ቤት ጽድቅ ብለን ሳይሆን ከነሙሉ ያንቺ ልጅነት ክብራችንና ነጻነታችን ጋር ይህም የሚፈጥረውን የባለቤትነት ስሜትና ርካታ ተላብሰን መሆን ይኖርበታል። አንድ ቀን ለዚሁ ተብሎ መንግስት እዚህ አገር ድረስ መጥቶ በጠራው ስብሰባ ያለኝን ልረዳ ሄጄ ነበር። ያዳራሹን በር የከበቡት አድር ባዮች ገና ለገና የሚነገረውን አርፎ አይሰማም ወይ ጥያቄ ይጠይቅ ይሆናል ብለው ከበር ላይ መለሱኝ። ገንዘቤን እንጂ ነጻነቴን አልፈለጉም። አቤት አድር ባይ ለመፈልፈል ያለሽ ችሎታ! ያላማራቸውን ሰው ሁሉ ከበር ሲመልሱ ግድቡን ጨርሰው የሚሰሩት እነሱ ይመስሉ ነበር። ያወጡትን ገንዘብ ያህል ብዙ እጥፍ መልሰው የሚመነትፉ ጀግኖች ናቸው ይህን የሚሰሩት።

ለማንኛውም ልማት ጥሩ ነገር ቢሆንም ልማት ሁሉ ህዳሴ አለመሆኑን ከሰሙሽ ንገሪ። የጥሩ ነገር ስም ማበላሸት ሳያስፈልግ ሊሰራ የሚቻለውን መስራት ይቻላል ብለሽ በያቸው። አንቺ ኮ ገና እምቦቀቅላ ልጆቿን ከባርነት ላልተናነስ ግርድና አረብ ሀገር ልካ የምታስቃይ አገር ነሽ፤ ወጣት የተባለ ሁሉ ስደትን መንግሥተ ሰማያት አርጎ ይሚመለከትባት ሀገር ነሽ፤ ያስተማረቻቸውን ሊቃውንት ሁሉ ለባዕድ ሲሳይ በገፍ የምትገብር ሀገር ነሽ፤ የዘመኑ የሳይንሰና ቴክኒዎሎጅ ምንጭ የሆነውን የኢንተርኔት መረብ በማዳረስ ካፍሪካ ግርጌ የቆምሽ አገር ነሽ፤ ሰው በተናገረውና በጻፈው ነገር አሸባሪ እያሰኘሽ የምታሳስሪ አገር ነሽ። አሁን ዶሮን በሬ ነሽ ብለው በመጫኛ ቢጥሏት ምን ይጠቅሚታል? የባዕድ ጽንሰ ሀሳብና በፈረንጅ ቋንቋ መጠቀም ካለሸበት ይሚያንፏቅቅሽ አይመስለኝም። ከበርቴዎችሽና ባለስልጣኖችሽ ሚስታቸው ስታረግዝ እዚህ አገር እያመጡ እንደሚያስወልዱ ታውቂያለሽ። ልጃቸውን ያን ሁሉ ንብረታቸውን አውርሰው የተንቀባረረ አገልጋይ ዜጋሽ እንደማድረግ ገና ሳይወለድ ሲያስቀሙሽ አየሻቸው? እነሱ ለልጃቸው ያልተመኙትን ሀገር ታዲያ ማን ይመኝ እምዬ? ለመሆኑ ምን ሆነው ነው ይህን የሚያደርጉት? መቼም በደህናቸው አይደለም። በቀደም ለት አንድ በዚህ አገርና ባውሮፓም እንደራሴሽ (አምባሳደርሽ) የነበረ የተከበረ ሰው እዚሁ የኔ ስደት አገር አንድ የመንግስት በጎ አድራጎት ድርጅት ቢሮ ውስጥ ከሚስቱ ጋር ተሰልፎ አየነው ብለው ሰዎች ነገሩኝ። ክብርሽ እዚህ ድረስ ወርዶልሻል። ቀደም ብሎ ሚስቱንና ልጆቹን በጎን ጥገኝነት አስጠይቆ ከመንግስት ፈቃድ ጠይቆ በሰላም ነው አሉ የመጣው። እዚህ በኛ ላይ በውሸት ሳይቀር ሲያሳብቅ የከረመ ሰው እንደነበር ካዝረከረከው ዶሴ ላይ አንድ ጊዜ አይቼ ነበር። ምን ምን አይነቱን ሰው ነው እየመረጥሽ የምታግበሰብሽው? አሁን ይኸ ማ ይሙት ህዳሴ ላይ ያለች አገር ባህሪ ነው?

ሌላም እንድ ነገር ልንገርሽ። ይህን ከመንግሥት ጋር ጣጣ ያለውን ሁሉ አሸባሪ ማለትን ተዉት በይ። ዘላለም ተከባብረው የኖሩ ሙስሊምና ክርስቲያን ልጆችሽን ለማጣላት የሚደረገውን የሰይጣን ስራ አቁሙ በይ። በነገሩ ውስጥ እኔ ምንም የሽብር ነገር አላየሁም። ይህ የኔ የስደት ሀገር ያሸባሪ ችግር የገጠመው ነገሩ ወዲህ ነው። ክንፉ ረጂም ስለሆነ ዓለምን ከአጽናፍ አጽናፍ ይነካል። ጡንቻውም አንዳንዴ የሚያርፍበት ቦታ ነገር ያመጣል። አውሮፓዎቹም እንደዚያው ነው። አንቺ የለት ጉርስ ማሟላት ያቃተሽ ድህነት ያሸበረሽ አገር ነሽ። ግዥዎችሽ አርፈው ከተቀመጡ አንቺን ለማሸበር እንቅልፍ አጥቶ የሚያድር ባዕድ ያለ አይመሰለኝም። የውስጥ አምባጓሮኛ ሁሉ ደሞ አሸባሪ አይደለም። ከታሪክሽ ታውቂዋለሽ። መፍትሔው የከፋቸውን ሁሉ ሰብስቦ መነጋገርና መፍትሔ ማበጀት እንጂ አሸባሪ ማለት አጉል ፈልፈላ መጥራት ነው። ጦም ውሎ ማደርንና እንደነገሩ ኖሮ መሞትን ያህል ሽብር ያለብሽ ሀገር የገዛ ልጆችሽ ምን ሁኝ ብለው ያሸብሩሻል። ይህን ነገር ብዙ መዘዝ ሳያመጣ አስቁሚ። ነገሩ የሚፈታው ሰው በማሰርና በመግደል ሳይሆን በመወያየት ነው። አየሽ መወያየት ሰው አይገልም። በመጋደልና በስቃይ መንገድ ያለውን ሁሉ ሞክረሽዋል። የውይይቱን መንገድ ደግሞ ለለውጥ ያህል እንዲሞከር ምከሪ።

በይ እናት አለም ስለጮኩብሽ ይቅርታ። ዉቢቱ ለምለሚቱ እያሉ የሚፎግሩሽ ብዙ ስለሆኑ ነው እኔ የምር የምሩን የነገርኩሽ። ከፉሽን እንዳልሰማ እዚሁ ሆኜ እጸልይልሻለሁ። ካላንቺ የማይሞላ ተልቅ ጉድጓድ አሁንም በሆዴ ውስጥ አለ። ከርቀት ተለቅሶ የማይወጣ እምባ አጠራቅሜበታለሁ። ከወለደችኝ ጀምሮ ነጋ ጠባ ተንበርክካ፣ አምላኳዋን አስቸግራ በህይወት የምንሳፈፍበት ክንፍ ከእግዚአብሄር ያሰጠቸኝን የናቶች ሁሉ እናት፥ ቀዥቃዣው አንድ ልጇ ዘላለም አደጋ ውስጥ በተማገድኩ ቁጥር በክንፋቸው ከልለው የሚያወጡኝ መላዕክት ልመና ከቤተ ክርስቲያን በር ላይ የምትገኘውን እናቴን፥ የደግነትና የፍቅር መምህርቴን፣ የርህብ መድሃኒቴን እማዬን ቀብሯ ላይ ተንበርክኬ ሳላለቅስላት ስለቀረሁ ፈስሶ ያላለቀ እምባ በሆዴ ጉድጓድ አለ። እንኳን ህዝንና ለቅሶ ደስታም በስደት አያምርም አይደል።

ሰላምና ፍቅር አብዝቶ ያስፍንብሽ። አልረሳሽም እናትዬ፥ ብረሳሽ ቀኝ እጄ የምትሰራውን ትርሳ።

Fekadeshewakena@yahoo.com

## በሳውድ አረቢያ በኢትዮጵያውያን ላይ የደረሰውን ጥቃት የሚቃወሙ ሰልፎች . . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

ሰልፈኞቹ የሳውዲ መንግስት ተገቢውን ይቅርታ እንዲጠይቅ፣ በዜጎች ላይ ላደረሰው በደል ካሳ እንዲከፍልና እንዲሁም ወንጀለኞችን ለፍርድ እንዲያቀርብ የሚጠይቁ ሰላማዊ ሰልፎች ጠይቀዋል።

ሳዑዲ አረቢያ ዉስጥ ከ20 ሺ በላይ የሚሆኑ ኢትዮጵያውያን ወደ አገራቸው ለመመለስ እየተጠባበቁ ቢሆንም፣ ከሰሞኑ የሳውዲው ንጉስ የመኖሪያ ፈቃድ የሌላቸውን የውጭ አገር ዜጎች የማስወጣቱ ሂደት ተጠናክሮ እንዲቀጥል የሰጡት አዲስ ትእዛዝ በሌሎች የአገሪቱ ከተሞች በሚገኙ ኢትዮጵያውያን ላይ ሌላ አደጋ ይዞ ይመጣል ተብሎ ተሰግቷል። ከውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት ባገኘነው መረጃ መሰረት በሳውዲ አረቢያ የመኖሪያ ፈቃድ የሌላቸው ከ180 ሺ ያላነሱ ኢትዮጵያውያን ይገኛሉ። የኢትዮጵያ መንግስት እስካሁን ድረስ 8 ሺ የሚሆኑ ኢትዮጵያውያንን ማምጣቱን ገልጿል። የተጠቀሰውን አህዝ ለማረጋገጥ ለውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ቴውድሮስ አድህኖም ብንደውልም፣ ስብሰባ ላይ መሆናቸውንና፣ አብዛኛው መረጃ ከኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ማግኘት እንደምንችል ገልጸውልናል።

### ዛሬም ታለቅሳለች! (በፊልጶስ)

ትላ'ትናም - ዛሬም
ቁማም - ተቀምጣም
በውኗም - በህልሟም፤
እምባ እያዘነበች
ደም እያፈሰሰች፤
ሁሉንም እያየች
ዛሬም ታለቅሳለች። …

"ረስታ - ተረስታ
በራሷ ላይ ዘግታ፤
ከጥዋት እስከማታ
እንቅልፏን ተኝታ"።
ተብሎ ተወርቶባት
ለብዙ ዘመናት
ታሪክ ተጽፎባት፤ …
እሷ ግን፣ እሷ ናት
ዓለም የሚያያት፤
እምባ እያዘነበች
እህህ … ትላለች
ትንሰቀሰቃለች፤
ሁሉንም እያየች
ዛሬም ታለቅሳለች። …
ተማፅኖ ተማሎ
ተገዝቶ ምሎ
ገ'ሎና አስገድሎ፤
"ለ'ርሀብ - 'ርዛትሽ
ለልመና - ፅናትሽ
ለፍትህ - እጦትሽ
ለሰላም - ለፍቅርሽ፤
መድሀኒት አውቃለሁ
እኔ እሻልሻለሁ"፤
ብሎ የሚገባው
እምባዋን ሊጠርገው
መፍሰሱን ሊያቆመው፤ …
ጭራሽ አብሶባት
ሀዘን ደራርቦባት፤
ማቁን አስለብሶ
አመድ አስነስንሶ፤
ሰይፉንም አስታጥቆ
ደረት አስደልቆ፤
ዙሪያ እያስረገደ
ሙሾ እያስወረደ፤
ሰድቦና አሰድቦ
ክብሯንም አዋርዶ፤
እዬዬ … አሰኝቶ
የዛሩን ተወ'ቶ፤
ደም - ከደም አቃብቶ
ምሱንም አግኝቶ፤
ይሄዳል ማን ቀርቶ
አስለቃሽ ተከቶ። …
እሷ ግን፣ እሷ ናት
ዓለም የሚያያት። …
አለቀልሽ ሲሏት
ነፍስ እየዘራባት፤
የነቁጥ ጭላንጭሊት
ደ'ሞ ሲታይባት፤
"የልጆቿ" ልክፍት
አዙሮ ሲጥላት
ጨለማ ሲያስገባት፤
ስትደነባበር …
ስትውተረተር …
ጣር ሲያጣጥራት …
ሺ' ዘመን አለፉት።
ትውልድ ሁሉ ዘንግቶ
ሰው ምሆኑን 'ረስቶ፤
ማንነቱን አ'ቶ
አደራውን ከድቶ፤
መፍትሄ የጠፋው
ምን ይሆን መጨረሻው፤
ደም አስለቃሽ፣
ያለመታከቱ
ያለመማሩ፣ ከታሪክ -
ከትላንቱ
የ'ሷም አይን
ያለመጥፋቱ።